ቀን ጥር ፳፩÷፳፻፰ ዓ.ም

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤**
**አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**
**በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥**
**ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥**
**ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡**
**ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።**

እጅግ ለተከበርከዉና ለምትወደደዉ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይና ዋና ተጠሪ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ!

ከተከበሩትና ከተወደዱት እንዲሁም ከተመረጡት ኪዳናዉያትና ኪዳናዉያን የቅዱሱ ኪዳን ቤተሰብህ ጭምር እንዴት ሰንብታሃል? እኔ ቸሩ እግዚአብሔር ከነእናቱ ድንግል ማርያም ጭምር ምስጋና ይድረሰዉ እጅጉን ደህና ነኝ፡፡

ጋሽዬ! ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት የተላለፈዉን አስረኛዉ የዐዋጅ ቃል በተመስጦና በኀዘን ስሜት አነበብኩት፡፡ ትዉልዱ በተደጋጋሚ ተግሳጽና ማስጠንቀቂያ በተለያየ ጊዜ ቢደርሰዉም ሊሰማና ሊቀበል አልቻለም፡፡ እግዚአብሔር እም እመቤታችን ድንግል ማርያም በተደጋጋሚ ልጆቿ ከጥፋትና ከመደምሰስ እንዲድኑ በእዉነተኛ አገልጋይ ላይ አድራ ቃል በቃል ከእግዚአብሔር የሆነዉን መልእክት ብታስተላልፍም እንኳን ሌላዉ ዓለም ቀርቶ በስሟ የተጠሩት ኢትዮጵያዉያን እንኳ ሊቀበሉት ቀርቶ ምንድነዉ ብለዉ ሊመለከቱት ሆነ ሊጠይቁ አልቻሉም፡፡ በጣት ከሚቆጠሩት ኪዳናዉያንና ኪዳናዉያት በስተቀር፡፡ በተለይ በተለይ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይና አገልጋይ ነን የሚሉት ሳይቀር ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚተላለፈዉን የእግዚአብሔር የእዉነት ቃልና መልእክት አለመቀበላቸዉና አለመፈለጋቸዉ እጅጉን ያሳዝናል፤ ያስተዛዝባል፡፡ ለዚህም ነዉ እመ አምላክ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመልእክቷ በግልጽ፡ በአሰረኛ የዐዋጅ ቃል ገጽ ፴፯ ላይ

**" ራሷን፡ በሚያሳዝን ኹኔታ በማዋረድ፡ በአራተኛው ምእተ ዓመተምሕረት፡ በግብፅ (በቅብጥ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተችና የእርሷ ቅርንጫፍ ኾና፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተቋቋመች፡ ራሷን፡ በይፋ የምታስታውቀው፥ እስከዛሬና ዛሬ፥ ወደፊትም፡ በዚህ**

መልኩ ልትቀጥል የወሰነችበት፡ ይህ አቋሟም፡እስካኹን፡ ፩ሺ፯፻ ዓመታትን ያህል ያስቆጠረ ስለመኾኑ፡ በራሷ አረጋግጣ የሚነገርላት፥ ሰዎችም፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማለት የሚጠሯት አይደለችም፣ ይህች፡ የእኔዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት። ይህን እውነታ፡ በተጨማሪ ሓተታ ማብራራቱ፡ እጅግ አስፈላጊ ይኾናል። ይኸውም፦-"የቃል ኪዳን ልጆቼና የርስት ጕልት ሕዝቤ" የኾናችሁትን፡እናንተን በማዳን ፋንታ፥ የእኔ፡ የኢትዮጵያ የኾነውንም ኹሉ፡ አጽንታ በመጠበቅ፥ አስፋፍታም በማሳወቅ ፋንታ፡ እንዲህ፡ ለግብጣዊቱ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን፡ ባሳት ተገዢነት ምክንያት፡ ያን ኹሉ ኃላፊነቷን በመተው፥ መልካሙንም ኹሉ፡ከአይሁዳውያኑ የኦሪት ሕግ እና ከግብፃውያኑ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንደተገኘ በማስመሰል፡ የእርሷ የራሷ የኾነውን ኢትዮጵያዊነትን ግን፡ ፈጽማ ሠርዛና ክዳ፡ በዚያ ቦታ፡ ኦሪታዊነትንና ኦርቶዶክሳዊነትን ተክታና አጽድቃ የኖረችውና አኹንም፡ እየኖረች ያለችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፣

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።" በማለት ቤተክህነቱ በፈጸመዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ አምልኮ ምንዝርና ምክንያት ጸጋዉና ማንነቱ ተገፎ ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥትነት የተለየዉ፡፡

ሴላዉ እመቤታችን ድንግል ማርያም ምንም እንኳን ብትቆጣና ብታዝንብንም አሁንም እንደ እኛ ፍጡሮቹ ሰዎች በትዉልዱ ተስፋ ሳትቆርጥ በእግዚአብሔር እናትነቷና ፍቅሯ እንዲሁም ርኅራኄዋ

" ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእኔ በለበሰው ፍጹም ሰውነቱ በተቀበለው፡ ሕማማተ-መስቀሉና ጽዋ-ሞቱ፡ ዘለዓለማዊዉን ሰላም፡በድል አድራጊነት ያስገኘላችሁ መኾኑ ነው፧

ውድ ልጆቼ ስለኾናችሁ፡ የቀደሙት ወገኖቻችሁ፡ እንደእናንተ እንደዛሬዎቹ፡ የምክርና የማስጠንቀቂያ ቃሌን ለመስማት ባለመፈለጋቸው፡ ባለፉት ዘመናት ሲደርስባቸው የነበረውን፡ ያን የመሰለው አሠቃቂ ጥፋት፡ ዛሬ ደግሞ፡በእናንተ ላይ እያንዣበበ፥ እየደረሰም ስላየሁት ነው፧

ብትሰሙኝም፥ ባትሰሙኝም፡ ለእናንተ ልጆቼ ካለኝ፡በርኅራኄዬና በምሕረቴ ከተመላው፡ ከነፍሳዊው፥ ከሥጋዊውና ከመንፈሳዊው የወላጅነት ፍቅሬ የተነሣ፡ ዝም ብዬ መመልከቱ አላስችል ስላለኝ ነው። አዎን! እኔማ፡ እናንተ፡ በሰውነት፡ ለዘለዓለም፡ በመልካም ሕያዋን ኾናችሁ ትኖሩበት ዘንድ፡ አስቀድሜ፡ ይህን ፍጹም ያማረና የተሟላ ፍጥረተ-ዓለም፡ በጌታዬ በእግዚአብሔር አብና በልጄ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በሕይወቴ በእግዚአብሔርመንፈስ ቅዱስም ተዋሕዶ ያዘጋጀሁላችሁ፡ ፈጣሪያችሁ ነኝ። አዎን!

እናንተን፡በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ በመልካችን የፈጠርናችሁና ከእኛ፡ ከመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፡ እንደ አንዳችን ለመኾን የበቃችሁበትን፥ የገናናው ክብራችን ተሳታፊዎች ትኾኑ ዘንድ፡ የምንነት አካላችንን አጐናጽፈንና የማንነት ባሕርያችንን አቀዳጅተን ያስገኘናችሁ ነን። እንዲህ፡ ለእናንተ ስንል፡ በእግዚአብሔር አብ'ነትና በእግዚአብሔር እም'ነት፥በእግዚአብሔር ወልድነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነት፥ በመጨረሻ፡ በድንግልማርያም የሴትነት ጾታና በኢየሱስ መሲሕ የወንድነት ጾታ፡ የእናንተ አድርገን በሰጠናችሁ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ሳይቀር፡ በዚህ "እኔነት" እና "እኛነት"፡ለፍጥረታችን የተገለጽን ነን። ከዚህ የተነሣ፡ መልካሙና ቸሩ ፈጣሪያችሁ ብቻ ሳልኾን፥ የዘለዓለም አባታችሁና እናታችሁ፥ ካህናችሁና መቅደሳችሁ፥ ንጉሣችሁና ንግሥታችሁ፥ አገራችሁና ነፃነታችሁ፥ ሃይማኖታችሁና መንግሥታችሁ የኾንሁት፡ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።

ጥንቱኑ፡ በዚህ ኹኔታ የፈጠርናችሁ እኛ፡ የቀድሞዎቹም ኾኑ የኋለኞቹ ወገኖቻችሁና እናንተ ጭምር፡ ያማሰናችሁትን [ያበላሻችሁትን] እና ያቃወሳችሁትን፥ያጣመማችሁትንና ያጠፋችሁትን፥ ያሳደፋችሁትንና ያረከሳችሁትን ኹሉ፡ማንነታችሁንና ምንነታችሁን ሳይቀር፡ በድንግል ማርያም የትስብእት መድኃኒትነቴ እናበኢየሱስ መሲሕ የትስብእት ቤዛነቴ፡ አድሰንና አስተካክለን፥ አቃንተንና አልምተን፥አንጽተንና ቀድሰን፥ ወደቀደመው ድንግል አካልነቱና ንጽሐ ባሕርይነቱ መለስነው!እኛ፡ እናንተን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንን፡ እንዲህ አድርገን፡ ለእኔነትናለእኛነት ያበቃናችሁ እኮ፡ በዘለዓለማዊነት በሠራነው ዓለምና ሥርዓት፡ እኛንመስለሳችሁ፡ በፍጹሙ መልካም ሕይወት እንድትኖሩ እንጂ፡ ከሥጋዊው አእምሮአችሁ ከፈለቀው፡ ከዚህ የተሳሳተ እምነታችሁና ክፉ አስተሳሰባችሁ የተነሣ፡ ይኸው አኹን እንደምታዩት፡ ፍጻሜው፡ "ሞትና ዕልቂት" ለኾነው ህልውና፡ እየራሳችሁን፡እንድታዋርዱና እንድትዳርጉ አልነበረም፤ አይደለምም።

" ገጽ ፲፰ በማለት ነዉ ርኅራኄዋንና ማንነቷን ጭምር የገለጸችልን፡፡

ከዚህ በማስከተል በዉስጤ የሚመላለሱትን ሓሳቦችንንና ጥያቄዎችን አቀርባለሁ፡፡

ሀ. እመቤታችን ባለፋት የዐዋጅ ቃል በእግዚአብሔር እም'ነቷ እስከምትገለጽ ድረስ በኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት በቅድስት ቤተክርስቲያን እዉቀት ያለዉን ማንነቷንና ክብሯን እንዲሁም በተለየ ሁኔታ በተገለጸልኝ የሕወታችን ምስጢር ቁልፍ መሆኗን ብቻ ነበር የማዉቀዉ፡፡ ይኸዉም የአምላክ እናት፣እመ እግዚአብሔር፣ ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች፣ የአደራ እንታችን፣ አማላጃችን፣ ቅድስት ድንግል ማርያም ወዘተ የመሳሰሉት ሲሆን፤ በነፍሴ ደግሞ መምህር ሆነ ሊቃዉንት ሳያስተምረኝ ሳይገባኝ እርሱ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በገለጸልኝ መሰረት የሕወታችን ምስጢር ቁልፍነት እንዲሁም ሁሉን እንደ እግዚአብሔር ማድረግ እንደምትችልና በሰማያትም እግዚአብሔር በተገለጸበት ብርሃናዊ ባህርይ ተገልጻ እንደምትመሰገን ነዉ፡፡ ታዲያ ራሱ እግዚአብሔር በሕሊናዬ የገለጸልኝ እዉነት በአንተ በኩል እግዚአብሔር ለትዉልዱ በዐዋጅ ቃል ካስተላለፈዉ እዉነትና መልእክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ አገኘዉት፡፡ ያ ብቻ አይደለም እመቤታችን ቅድስት

ድንግል ማርያም እግዚአብሔር እም መሆኗን በደንብ ገባኝ። እግዚአብሔርም ለሰዉ ልጆች በእግዚአብሔር አብ( አባትነት)ና በእግዚአብሔር እም( እናትነት)፣ በእግዚአብሔር ወልድ( በልጅነት)፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ(በመንፈስነት) ስም መገለጹንና በአንድነትና በሦስትነት እንደሚመሰገንና እንደሚመለክ በሚገባ አስተዋልኩ።

ታዲያ እግዚአብሔር እም ያስተላለፈችዉን መልእክት የዓለም ሕዝብ ሁሉ በሚገባ ቢያነበዉ የመጀመሪያ ተቃዋሚና አዉጋዥ የሚሆኑት ከኪዳናዉያንና ከኪዳናዉያት እንዲሁም እግዚአብሔር በቅንነታቸዉና በእዉነተኛነታቸዉ ለተለየ አገልግሎት ከመረጣቸዉ አገልጋዮችና ምእመናን ዉጭ ያሉት እንደ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ እንዲሁም  እንደ አይሁድ ካህናት ግብዝነት የተላበሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት "አገልጋይና ምእመን" ነን የሚሉት ናቸዉ። ምክንያቱም እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች ምንም እንኳን ለጊዜዉ ከሚያዉቁት እዉቀት ዉጭ ያለዉን ሙሉ እዉቀትና የእግዚአብሔር መልእክት ግር ቢላቸዉና በሕሊናቸዉ ጥያቄ ቢያስነሳባቸዉ እንኳ ዉስጣቸዉ ቅንነትና እዉነተኛነት የተላበሰ ስለሆነ ሕሊናቸዉን እንደ ምሁሩና ሊቁ ፈሪሳዊዉ ኒቆዲሞስ ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፈዉ ስለሚሰጡ እርሱ እግዚአብሔር ምስጢሩን ይገልጽላቸዋል፣ እዉነታዉን ያሳዉቃቸዋልና ደፍረዉ እግዚአብሔርንና እመቤታችን ድንግል ማርያምን  አይቃወሙም፤ ከእግዚአብሔር የሆነዉን አያጣጥሉም። ይልቁኑ ግልጽ እንዲሆንላቸዉ ጥያቄና ማብራሪያ ይጠይቃሉ እንጂ። በተቃራኒዉ ደግሞ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ ብቻ ስለሚያገለግሉና ስለሚያምኑ የዲያብሎስ መንፈስ በቀላሉ በሕሊናቸዉ ስለሚነግሥ ከእግዚአብሔር ወይንም ከእመቤታችን የሆነዉን ሙሉ እዉነት ለመቃወምና ለማዉገዝ ከተቻላቸዉ ጌታን ለግፍ ድብደባና ስቅላት አሳልፈዉ እንደሰጡት ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት ከመወንጀልና ማንኛዉንም ግፍ ከማስፈጸም ወደ ኋላ አይመለሱም።

ይህን ሐሳብ ለማንሳት የፈለኩት በኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት በቅድስት ቤተክርስቲያን እንደ ግለሰብ እግዚአብሔርን በመፍራትና በእዉነትና በመንፈስ በማምለክ ሕይወት ዉስጥ ያሉ አገልጋዮችና አማኞች እንዳሉ ይታወቃል። ነገር ግን በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት በኩል የሚተላለፈዉን መልእክት ሆነ እዉቀት የማግኘት እድሉ የላቸዉም። ያ ብቻ አይደለም  የጸሐፍት ፈሪሳዉያን እንዲሁም አይሁድ ካህናት ሕይወት የተላበሱ ሳይገባቸዉ በእዉነተኛዉ መንፈሳዊ ወንበር ላይ በተቀመጡ አስመሳይ አገልጋዮች ስብከትና ማስጠንቀቂያ እነሱ ከሚሉት ዉጭ የማንንም መልእክት ሆነ ትምህርት እንዳይሰሙና እንዳይቀበሉ ሕሊናቸዉን ስለዘጉባቸዉ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ " ከእኛ እዉቀትና አገልግሎት በላይ ለአሳር"  በሚሉ ትንሿ  እዉቀታቸዉና አገልግሎታቸዉ ጣዖት

በሆነባቸዉ በእዉቀት አገልጋዮችና አማኞች ዘንድም በአንተ በኩል እግዚአብሔር ወይንም እመቤታችን ድንግል ማርያም የሚያስተላልፉት መልእክት ሆነ እዉነት ተቀባይነት እንደሌለዉና ራሳቸዉን ለሙሉ እዉነታ አገልግሎት እንደማያበቁ ይታወቃል፡፡ ያ ብቻ አይደለም የእግዚአብሔርን እዉነት ከመቃወምና ከማጣጣል እንደማይመለሱ ይገመታል፡

ሌሎች በዘልማድ እንደ ሥጋና ደም ስሚታቸዉ የሚመላለሱ ሕዝቦች ቀደም ሲል በእግዚአብሔር የለሽ ሥርዓትና ትምህርት ሕሊናቸዉ ስለተበከለና ስለተመረዘ፤ በቅርብ ደግሞ በዚህ በተበከለና በተመረዘ ሕሊና ዉስጥ ዲያብሎስ ነግሦ በዘረኝነትና በጎጠኝነት እንዲሁም በጥላቻና በበቀል ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለሱ ስላደረገ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ሌት ተቀን ስለገንዘብ ብቻ እንዲያስቡ ተስፋቸዉን ገንዘብና ምድራዊ ቁሳቁስ ላይ ብቻ አድርገዉ እንዲኖሩ እንዲሁም በተለያየ መንገድ ሌት ተቀን በተለያየ ወሬና ትእይንት ጨዋታ ትዉልዱ እንዲደነዝዝ ስለተደረገ ይኸዉ ከኖኅ ዘመን በከፋ መልኩ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ እንመላለሳለን፡፡ በዚህም ምክንያት እንኳን ለእግዚአብሔር መልእክት ቦታ ሰተን ልንሰማና በእዉነተኛ ንስሐ መመለስ ቀርቶ እለት እለት በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት እየጨመርን ራሳችንን እንደ ኖኅ ዘመን ለመደምሰስ እያዘጋጀን እንገኛለን፡፡ የሚያሳዝነዉ ደግሞ ሕያዉ በሆነችዉ ነፍሳችን ላይ የሚፈረደዉ ፍርድ ከእነሱ የባሰ መሆኑ ነዉ፡፡ ምክንያቱም እነሱ የነገረ መስቀሉን ድኅነት አላዩም አልሰሙም፡፡ እኛ ግን ይኸዉ ለሁለት ሺህ ዓመት እየሰማን ሕሊናችንን በማደንደን ነዉ በዓመፃችንና ክህደታችን እንዲሁም በአምልኮ ምንዝርነታችን የጸናነዉ፡፡

ከላይ የገለጽኳቸዉ ራሳቸዉን እንደ እዉነተኛ አገልጋይና አማኝ የሚቆጥሩ ግለሰቦች በአንተ በኩል እመ አምላክ ቃል በቃል ያስተላለፈችዉን መልእክት ቢመለከቱ ዋና ተቃዋሚና አጣጣይ እንደሚሆኑ ጥርጥር የለዉም፡፡ ምክንያም ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ያላቸዉ እዉቀት " አማላጅ ናት፣ ፍጡር ናት፣ የጸጋ ስግደት ብቻ ነዉ የሚገባት፣ የጌታ እናት ናት" ብቻ የሚለዉን ስለሆነ እግዚአብሔር በጊዜዉ አንድነቱንና ሦስትነቱን በሐዲስ ዘመን በግልጽ እንደገለጸ ሁሉ አሁን ደግሞ ራሱን በእግዚአብሔር እም'ነት ሲገልጽ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናት ለእግዚአብሔር የቀኑ መስሏቸዉ "ዘራፍ አካኪ እንዴት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር እም ትባላለች? እንደ እግዚአብሔር ትቆጠራለች? እንዴት የአምልኮ ሰግደት ይሰገድላታል? እንዴት ቅድሰት መለኮታዊት ትባላለች? እንዴት ፈጣሪ ትባላለች" በማለት እንደሚቃወሙና " ይህ ክህደት ነዉ፣ ይህ ሃይማኖታችንን ያፋልሳል፣ ይህ ከእግዚአብሔር አይደለም.. ወዘተ " ከማለት አይመለሱም፡፡ በዚህ አጋጣሚ በዚህ አስተሳሰብ ዉስጥ እዉነተኛ የእመቤታችን ድንግል

ማርያም ወዳጆችና አፍቃሪዎች ካላችሁ ስለምን ይሆን መንፈስ ቅዱስ በቀረባችሁ ጊዜ የእመቤታችን ፍቅር በዉስጣችሁ የሚነደዉና አመስግናችኋት የማትጠግቡት? በቅዳሴዉ፣ በማኅሌቱ፣ በሰዓታቱ፣ ባጠቃላይ በመዝሙሩ እንድትመሰገንና እንድትገን እግዚአብሔር ስለምን አደረገ? የእርሷ መመስገንና መግነን የእርሱ የእግዚአብሔር መመስገንና መግነን ስለሆነ አይደለም ወይ ስንት ቅዱሳን፣ ጻድቃን አመስግነዋት አመስግነዋት ስላልረኩ የምናመሰግንበት ቃላት አጠረን የሚሉት? በተቃራኒዉ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የራቃቸዉ ከጸጋ እግዚአብሔር የተለዩ ሰዎች እርሷ ስትመሰገንና ስትገን ስለምን ይሆን የሚቃወሙት? ስለምን ይሆን እንኳን ማመስገን አይደለም ስሟ እንዲጠራ የማይፈልጉት? አዎን ዲያብሎስ የሕወታቸዉ ምስጢር ቁልፍ እርሷ መሆኗን ስለሚያዉቅና ትዉልዱን ከእርሷ ለየ ማለት በእርግጠኝነት ከእግዚአብሔር እንደለየ ስሚያዉቅ ነዉ በእነዚህ ሰዎች ሕሊና ላይ በማደር ጥላቻና ተቃዉሞ የሚያመጣዉ፡፡

ወደ ሙሉ እዉነታዉ ስንመጣ እግዚአብሔር ራሱን እግዚአብሔር ወልድ (ልጅ)ተብሎ በኢየሱስ መሲሕ(ክርስቶስ) ስም እንደተገለጸ ሁሉ እግዚአብሔር እም ተብሎ በድንግል ማርያም ስም መገለጹን ነዉ፡፡ እንግዲህ ሙሉ እዉነትን የሚፈልግ ሰዉ ሕሊናዉን ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፎ ስለሚሰጥ ከእግዚአብሔር የሆነዉን እዉነት በሚገባ ይረዳል፤ ያስተዉሳል፡፡ እዉቀቱ ጣዖት የሆነበት ሰዉ ግን እግዚአብሔር ራሱ ተገልጾ ያለዉን እዉነት ቢያሳዉቀዉ አይቀበልም፡፡ ይልቁኑ ከተቻለዉ እግዚአብሔርን ከመቃወምና ከማሳደድ አይመለስም፡፡ ነገር ግን ባለማወቅ እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ ሕይወት የተሳበሰ ሰዉ በትንሽ ግሳጼ እግዚአብሔር ለሙሉ የእዉነት አገልግሎት ያሰልፈዋል፡፡ የተመረጡት ኪዳናዉያንና ኪዳናዉያት ደግሞ ሕሊናቸዉ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኝ ስለሆነ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሙሉ እዉነት ለመቀበልና ለማስተዋል አይቸገሩም፡፡ ምክንያቱም ሕሊናቸዉን ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፈዉ ሰተዋልና ከእግዚአብሔር የሆነዉንና ያልሆነዉን እርሱ መንፈስ ቅዱስ ያሳዉቃቸዋል፤ ይገልጽላቸዋልና፡፡ እኔም ሳይገባኝ እንደ በደሌና ኃጢአቴ እንዲሁም እንደ ደካማነቴና ተራነቴ ሳይሆን እንደ ቸርነቱና ምሕረቱ ለኪዳናዊነት ያበቃኝን እግዚአብሔር አብወእምን እያመሰገንኩ ሌሎች ወገኖቼም በእዉነተኛ ንስሐ ለኪዳናዊነትና ለእዉነተኛ ኢትዮጵያዊነት እንዲበቁ ጸሎቴና ምኞቴ ነዉ፡፡

ለ. ጥያቄዉ ደግሞ፡ እርሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም በተገለጸ ጊዜ አንድም ለእኛ አርአያ ለመሆን አንድም ፍጡሩን ሥጋ መልበሱን ለማጠየቅ ከእርሱ በላይ አምላክ ወይንም ፈጣሪ ወይንም እግዚአብሔር እንደሌለ እያወቀ እግዚአብሔር አብን "አምላኬ አምላኬ ስለምን ተዉኸኝ" ማቴ.፳፯÷ ፵፮ ብሎ እንደጠራ ቢታወቅም፡፡ የመስቀሉ የድኅነት ተግባሩን ከፈጸመ በኋላ ግን ራሱን "ያለዉና የነበረዉ የሚመጣዉም ሁሉንም

የሚገዛ ጌታ አምላክ- አልፋና አሜጋ እኔ ነኝ" ዮሐ. ፩÷፰ በማለት ነዉ እንደ ፈጣሪነቱ እንደ እግዚአብሔርነቱ እንደ ገዥነቱ ራሱን የጠራዉ፡፡ታዲያ በቃለ ዐዋድ ፲ ኛ ሳይ በገጽ፲፰ በአንቀጽ ፰ ሳይ እመቤታችን በእግዚአብሔር እም’ ነቷ በፈጣሪነቷ ራሷን ገልጻ ሳለና በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት መበላለጥ አንደሌለ እንዲሁም ጌታና ታዛዥ የሌለ መሆኑ እየታወቀ፤ እግዚአብሔር እም እንዴት እግዚአብሔር አብን "ጌታዬ" ልትለዉ ቻለች? ምክንያቱም እግዚአብሔር በአባትነት በእናትነት የተገለጸ አንድ የሆነ ስለሆነ "ጌታዬ" የሚለዉ አጠራር የሚያበላልጣቸዉ አያስመስልም ወይ? ወይስ እኔ በአግባቡ አልተረዳሁት አልተገለጸልኝ ይሆን?ጊዜ ስታገኝ እንደምታብራራልኝ እተማመናለሁ፡፡

ለ. እግዚአብሔር ወይንም እመቤታችን ድንግል ማርያም በሚያስተላልፉት ቃል በቃል መልእክት ሆነ የእዉነት ቃል ላይ ማንም ፍጡር ማሻሻያ ማድረግ ሆነ መለወጥ የማይቻል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ጽሑፉ የሚጻፈዉ በጸሐፊዉ እዉቀት ደረጃና በመቀመሪያ ስለሆነ በተሻለ አገላለጽና ቃላት ሆነ በተሟላ ሥርዓተ ነጥብና በተስተካከለ ፊደል ቢገለጽ መልእክቱን ሆነ ቃሉን አይለዉጠዉም፤ ይልቁኑ ጽሑፉን ሙሉ ያደርገዋል፡፡ ጋሽዬ! ታዲያ ካንተ በላይ ስለ ቃላት ሆነ ስለ ሥርዓተ ነጥብ እንዲሁም ስለ ፊደላት የሚጠነቀቅ ሰዉ የለም ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ የራሴ ሥጋና ደም ሐሳብ ይሁን የመንፈስ ቅዱስ አንተዉ ራስህ እንድትመረምረዉ እያልኩ የራሴን የማሃይምነት ሐሳብ አቀርባለሁ፡፡ ይኸዉም እግዚአብሔር እም ከእግዚአብሔ አብ ጋር አንድ እስከሆነች ድረስ ይኸዉም በእኛ እዉቀት ደረጃ አብ በወንድነት ጾታ እም በሴትነት ጾታ ከመጠራቷ ዉጭ በባሕርይም፣ በመለኮትም፣ በሕልዉናም አንድ ስለሆኑ "ጌታዬ" ከሚለዉ አጠራር ይልቅ "ባሕርዬ፣ ፍቅሬ" በሚለዉ አጠራር ቢጠራ ምን ይመስልሃል?

ጽሑፌን በዚሁ እቋጫለሁ፡፡ ኪዳናዉያትና ኪዳናዉያን ቤተሰቦችህን የጠበቀ ሰላምታ አቅርብልን፡፡ የተለመደዉ ጸሎትህ አይለየን ይላል እየወደቀ እየተነሳ ከዓለም ጋር የሚታገለዉ ታናሹ ወንድምህ ፈቃደ ሥላሴ፡፡

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም ወለመስቀሉ ክቡር

ጥር ፳፩÷፳፻፰ ዓ.ም